**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣት ክንፍ ( ኢወክንድ )**

**ሕዝባዊ ስብሰባ በዋሽንግቶን ዲሲ ኦክቶበር 2 ቀን 2011**

**በፓርቲው በኩል የተላለፈ አጭር መልዕክት**

**የተከበራችሁ ወገኖቻችን !**

የፓርቲው ወጣት ክንፍ ባዘጋጀው ስብሰባ ለመገኘት ጥሪውን አክብራችሁ ስለመጣችሁ በፓርቲው ስም ከፍ ያለ ምስጋና እናቀርባለን ! የወጣት ክንፍ አባላት ይህን ስብሰባ አዘጋጅታችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን በበኣላችሁ እንዲገኙ በማድረጋችሁ ፓርቲው የደስታመልዕክት ያስተላልፍላችኋል፡፡ይህ ስብሰባችሁም የተሳካ እንዲሆንላችሁ ድጋፉንና መልካም ምኞቱን ያቀርብላችኋል ፡፡

የዛሬው ስብሰባችሁ ፥ ኢትዮጵያ ሀገራችን በታሪኳ ውስጥ ምን ጊዜውም ቢሆን አጋጥሟት በማያውቅ በሞት-ሽርት መካከል በምትገኝበት ወቅት በመሆኑ ፥ልዩ ትኩረትንና ግንዛበቤ እንደሚያሻው በሚገባ ትገነዘባላችሁ ፡፡ ዛሬ ዜጎቿን በዘር በመከፋፈልና ሀገሪቱንም በመበታተን ፥ ታሪክ የማይረሳውን ብሄራዊ ወንጀል የሚፈጽሙት ወያኔዎች ፥ በትውልድም ሆነ በዜግነት ኢትዮጵያውያን መሆናቸው ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ባይሆንም፥በገዛ ሀገራቸውና ወገናቸው ላይ ይህ ነው የማይባል በደልና ጥፋት እየፈፀሙ ለመሆናቸው ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ መላው ዓለም ተገንዝቦታል ፡፡ ይህ የዓለም ሕዝብ ግንዛቤም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ መሪር አገዛዝ ለመላቀቅ ቢያደርገው ትግል ተገቢውን ድጋፍና ትብብር እንደሚያስገኝ ይገመታል ፡፡


EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

ኢትዮጵያ ሀገራችን የዓለም ሀገሮች ኅብረተ- ሰብ ኣባል በመሆኗም ከዓለም ዕይታ ውጭ ልትሆን እንደማትችል ብንገነዘብም ፥የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ፥ ነፃነቱንና የሀገር አድነቱን የሚፈታተነው የውጭ ኃይልም ሆነ የሀገር ውስጥ ከሀዲያን ሲገጥመው ተባብሮ ጠላቶቹን አሳፍሮ ድሉን እንደሚቀዳች አኩሪ ታሪኩ ይመሰክርለታል ። ዛሬም እንደትላንቱ ፥ የአሁኖቹን ከሀዲ የወገን ጠላቶች አስወግዶ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እንደሚመሰረት ኢሕአፓ አይጠራጠርም ። ያ ዕውን እስኪሆን ድረስም ፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የገባውን ቃልኪዳን ሳያጥፍ ፥ በኢትዮጵያ ነፃነት፥በሕዝቧ አንድነትና ብሄራዊ ጥቅሟ ሳይደራደር ትግሉን ይቀጥላል ። ይህን ሀቅ እያንገፈገፋቸውም ቢሆን ከማንም የበለጠ ወያኔዎቹ ይረዱታል ። ለዚህም ነው ፥ ኢሕአፓን ካላጠፋን ዕንቅልፍ የለንም ብለው የሚፍጨረጨሩት ። እነርሱ ይጠፏታል እንጅ ፥ ኢትዮጵያና ኢሕአፓ ግን አይጠፉም ። ይህም ለወገን የምሥራች ሲሆን ለኢትዮጵያ ጠላቶች ደግሞ መርዶ ነው ።

ስብሰባችሁን የምታካሂዱት፥ ሀገራችን ኢትዮጵያ በዘር ላይ ተመስርቶ የጥቂቶችን ጥቅም ብቻ ለማስጠበቅ ሲባል ተፈጥሮ በተዋቀረ ጎሰኛ አምባገነን መሪር አገዛዝ በወደቀችበት አሳዛኝ ወቅት መሆኑን በሚገባ ተረድታችሁታል ። ይህ ጠባብ ዘረኛ ቡድን ለአለፉት ሃያ ዓመታት በኢትዮጵያና በዜጎቿን ላይ የፈፀመውን ብሔራዊ ክህደት፥ ደባና ወንጀል፥ ከ ሀ እስከ ፐ በዝርዝር ስለምታውቁት ፥ በአሁኑ ወቅት ያን ለመዘርዘር አንቃታም። ምክንያቱም ይህንን ጠንቅቃችሁ በመረዳት በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ ስር ተደራጅታችሁ ለመታገል ቆርጣችሁ በመነሳታችሁ ነው ። ይህ የትግላችሁ ቃልኪዳን ማረጋገጫ የሆነውን ማኅተም የተረከባችሁት ከእናንተ በፊት ፥ የሀገራቸውን ነፃነትና ልዕዋላዊነት ፥ የሕዝቦቿንም ዕኩልነትና አንድነት እንዲሁም የዴሞክራሲ ሥርዓትን ለማረጋጋጥ መስዋዕት ከከፈሉት ቀደምት ጀግኖች ወንድሞቻችሁና እህቶቻችሁ ነው ። በመሆኑም ፥ ዛሬ ያንን የክብር ቃል-ኪዳንና ሀገራዊ አደራ ተረክባችሁ ለመታገል ቆርጣችሁ ስትነሱ፥ ከፍተኛ ብሄራዊ ኃላፊነት ተረክባችሁ ትግሉ የሚጠይቀውን ማነኛውንም መሥዋዕት ለመክፈል መዘጋጀታችሁ የተረጋገጠ ነው ። ይህም ሀቅ ፥ ኢትዮጵያ ሀገራችሁ አሁንም ቆራጥ ጀግኖች ልጆች እንዳላት ማስተማመኛ ብቻ ሳይሆን ፥ በዚህ ፈታኝና አስተዛዛቢ ዘመን የማይበገሩ ዜጎች ሀገር እንደሆነች ያስረግጥላታል ። ይህም በበኩሉ፥ትላንት በትግሉ ሜዳ የተሰዉት እነዚያአይበገሬ ቀደምት ሰማዕታት ትግሉን ተረክቦ አደራውን እያከበረ የሚሰዋ ትውልድ መተካታቸውን በአስተማማኝ ሁኔታ ያረጋግጣል ። እሳት ቢዳፈን ፥ የጠፋ ለሚመስላቸው ተስፋ ቆራጮችና ተንበርካኪዎችም፥ሀገራችን ኢትዮጵያዛሬም እንደጥንቱ ሀገረ- አናብስት እንደሆነች ሊገነዘቡት ይገባል ። ፓርቲያችሁ ኢሕአፓም ፥ ብኩርናውን በጭብጥ ምስር ሊለውጥ የማይችልመሆኑን ወያኔዎችና ተከታዮቻቸው ምንም ጊዜ ቢሆን ሊዘነጉት አይገባም ። የዛሬ አርባ ዓመት የተገባው ብሄራዊ የትግል ቃል ኪዳን፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድሉን እስከተቀዳጀ ድረስ ተጠብቆና ተከብሮ ትግሉን ይቀጥላል ።

ዛሬ ፥ሀገራችን የባዕዳንን ጥቅም በሚያስጠብቁ ከሀድያን ቅጥረኞችና ጊዜ እየጠበቁ በሚጎዷት የውጭ ኃይሎች ተቀዝፋ ተይዛለች ። የቅርብ ጎረቤትም ይሁን የዕሩቅ ዘመድ የሌላት መሆኗን ተረድተን ፥ አዳኞቿ እኛው ራሳችን ልጆቿ ብቻ መሆናችንን ኢሕአፓ በሚገባ ያውቃል ። ከዚህ ዕምነት በመነሳትም ፓርቲው የኢትዮጵያ አንድነት ኃይሎች ሁሉ በኅብረት የጋራ አንድነት በመመስረት ፥ በሀገር ውስጥ ትግላቸውን በቆራጥነት ለመታገል ከተዘጋጁ ተቃማዊ ኃይሎች ጋር ኅብረት ለመፍጠር አሳውቆ ፥ጥሪውን በይፋ ሲያስተላልፍ ቆይቷል ። አሁንም ለዚህ ሀገራዊ የአንድነት ትግል ዝግጁ ለሆኑት ሁሉ ጥሪውን በድጋሚ ያስተላልፋል ። ብቃትና ዝግጅት ካላቸው የአንደነት ኃይሎች ጋር ትግሉን ለማካሄድ ዝግጁ መሆኑንም እንደገና ያረጋግጣል ። ኅብረተ-ሰቡም ይህንን ተገንዝቦ አስፈላጊውን ትብብርና ርዳታ እንዲያደረግ አሁንም ጥሪያችንን እናስተላልፋለን ።

እናንት የፓርቲው ወጣት ክንፍ ኣባላትም ፥ ከፓርቲው ኣባላትና አካላት ጋር በመተባበር ይህን የፓርቲውን የአንድነት ኃይሎች ኅብረት የትግል ጥሪ በመገንዘብ አስፈላጊውን ዝግጅትና መሰናዶ እንድታደርጉ ይጠበቅባችኋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በመተባበር አብሮ ከተነሳ፥ የመከራ ገመዱን ባጭር ጊዜ በጣጥሶ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን በመመስረት፥ ሀገሩን ከጥፋት እንደሚያድን ጥርጥር ሊኖር አይችልም።

ይህን ስብሰባ በምታካሄዱበት ወቅት፥የፓቲው የትግል አልፋ-ኦሜጋ የሆኑትን ፅኑ መሠረታዊ ዕምነቶችና መርሆች አክብሮ መታገል እንዳለባችሁ ልትዘነጉት አይገባም ።እነኝህ መርሆች ደግሞ፥ ኢሕአፓን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ያስተሳሰሩት ጠንካራ ሀገራዊ ሀብል መሆናቸውን ምን ጊዜም ቢሆን በአዕምሯችሁ ውስጥ ቋሚ ሆነው የሚኖሩ ናቸው ። በረዥም የትግል ታሪኩ ኢሕአፓን ፥ ኢሕአፓ ያደረጉት መሠረታዊ ባኅርያትና የመርህ አቋሞች (ፕርንስፐልስ ) የሚከተሉት ናቸው።

- የኢትዮጵያን ብሔራዊ ነፃነትና ሉዓላዊነት ፥ የሕዝቧንም እኩልነትና መብት መጠበቅ ፥ ለዚህም ሲባል የሚከፈለውን መሥዋዕት ሁሉ እየከፈሉ መታገል ፥
- ለዴሞክራሲ ሥርዓት ፥ለህግ የበላይነት ፥ለፍትሕ- ርትዕ ፥ ለሰብዓዊ መብቶችና ለዜጎች ሉዓላዊነት እየታገሉ መሰዋት ፥
- እንኝህን መሠረታዊ ብሔራዊ ጥቅሞች የሚፃረሩትን መቃወም- መፋለም ሲሆን እናንተም ፥ የነገዋን ሀገራችሁን በኃላፊነት ስትረከቡ ፥ የኢትዮጵያን ጉራማሌነት በማክበር የዜጎቿን ታሪክ፥ዕምነት፥ባህልና ጠባይ በሚገባ አውቃችሁ እያከበራችሁ ፥ እንድትጠበቁ ፓርቲው አደራውን ያስተላልፍላችኋል ።

የሕዝብና የሀገር ፍቅር ፥ የኢሕአፓ ልዩ መታወቂያው መሆኑን መዘንጋት አይኖርባችሁም ::

ይህንን የተሳካ ባኣላችሁን እንድታከብሩ ለተባበሯችሁ ወገኖቻችን ሁሉ ፓርቲው ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርባል !

ኢትዮጵያ ሀገራችን አሁን ከገባችበት ማጥ ወጥታ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት

እስክትመሰርት ድረስ ኢሕአፓ ትግሉን ይቀጥላል !

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !!!